# ማሕበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ (ማ.ተ.ሰ.ኣ)

# UNION OF TIGREANS IN NORTH AMERICA (UTNA)

P.O.BOX 73736
Washington, DC 20056
utnaoffice@gmail.com

Tel. (202) 862-4367
Fax. (202) 265-8703
www.utna.org


## መንግስት የዜጎችን ደህንነት የመጠበቅ ሕገ መንግስታዊ ግዴታ አለበት!!

## በወቅታዊ የሀገራችን ሁኔታ ከትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን አሜሪካ የተሰጠ መግለጫ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት ከነበረችበት የሰላም፣ የልማት እና የዲሞክራሲ እጦት ወጥታ ለዜጎቿ የተሻለች እና በሕግ የምትመራ ሀገር ትሆን ዘንድ ብዙዎች መስዋዕት ከፍለዋል። ያ የመከራ ዘመን ከህይወት መስዋዕት በተጨማሪ የብዙዎችን አካል መጉደል የህዝቦች ከሀገር መሰደድ፣ መራብ እና መታረዝ ታልፎ በሀገራችን ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ለመትከል በቅተናል። ሀገራችን የምትከተለው ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ለመትከል የህይወት መስዋዕት እስከ መከፈል የደረሰ ውድ ዋጋ ከከፈሉ ህዝባዊ ማሕበራት (civic associations) ውስጥ፣ ማሕበራችን በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል።

ማሕበራችን በትግሉ ዘመን በነበረው ድርሻ ሳይወሰን፣ በሽግግሩ ዘመን ሀገራችን ኢትዮጵያ ሕገ መንግስታዊ ስርዓት እና ማሕበራዊ ፍትሕ የሰፈነባት እንዲሁም ዜጎች በእኩልነት እና በመፈቃቀድ ተከባብረው የሚኖሩባት ለማድረግ በተደረገውም የሽግግር ሂደት ላይ በስደት የኖሩ ከነበሩ የተደራጁም ያልተደራጁም ከተለያዩ ብሔር ተወላጆች ኢትዮጵያዊያን ጋር አጋርነት በመፍጠር በሂደቱ ንቁ ተሳታፊ እንዲኾኑ እንዲሁም የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ አግባብቷል፤ ተቀራርቦ ሰርቷል።

የህዝቦች የአብሮ መኖር እና መቀራረብ ሳንካ የነበረው ስርዓት ተወግዶ የሽግግር መንግስት ከተመሰረተ በኋላም ሕገ መንግስቱ መሰረት ያደረገ ስርዓት ተመስርቶ እንሆ 22 ዓመታት ተቆጥረዋል። በነዚሁ ዓመታት የጋራ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ማሕበረሰብ ለመፍጠር እና ሀገራችን ትታወቅበት የነበረ የኋላ ቀርነት እና ድህነት ምስል ለመቀየር በተደረገው የልማት ርብርብ አመርቂ ድል ተመዝግቧል። ሀገራችን ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ ላይ ትገኛለች። ነገር ግን ይህ ሀገራችን የተያያዘችው የሰላም እና ፈጣን የልማት ጉዞ በሕገ መንግስታዊ እና የፌደራል ስርዓቱ መከበር ካልታገዘ ታይቶ የሚጠፋ ብልጭታ ሊኾን ይችላል፤ በሂደትም ሀገራችን ልትወጣ ወደ እማትችለው ምስቅልቅል ሊከትን ይችላል። የሀገራችን ህዝቦች በእጃቸው ያስገቡት ራስን በራስ የማስተዳደር፣ በሀገራቸው ጉዳይ ላይ እኩል የመወሰን ስልጣን ያረጋገጠ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የሁሉም ህዝቦቻችን የጋራ ጥበቃ እና ከለላ ይጠይቃል።

ማሕበራችን ከላይ እንደተጠቀሰው የሀገራችን ልማት፣ ሰላም እና ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ሊጠበቅ የሚችለው ህዝባችን ከውስጥም ከውጭም ስርዓቱን ለማዳከም፣ ልማታችን እንዲስተጓጎል እና ሰላማችን እንዲናጋ የሚጥሩ የብልሹ አሰራር እና ጸረ ህዝብ አመለካከት ተዋናዮችን ነቅቶ እስከታገለ እና እስካጋለጣቸው ድረስ ነው ብሎ ያምናል። በዚህ ረገድ ህዝባዊ ማሕበራት፣ የሚዲያ ተቋሞች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና የሀይማኖት መሪዎች ትልቅ ሐላፊነት አለባቸው። ይህ ሲባል በተለያዩ እርከን የሚገኙ የመንግስት አካላት የሀገርን እና ዜጎችን ድህንነት የመጠበቅ ቀዳሚ ሕገ መንግስታዊ ግዴታ እንዳላቸው ስንዘነጋ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአንዳንድ የሀገራችን አካባቢዎች እየታየ ያለው የሰላም መድፍረስ፣ የዜጎች ድህንነት አደጋ ውስጥ መውደቅ እና የጸረ ህዝብ አመለካከት ዝንባሌዎች ማሕበራችን በቅርበት ሲከታተል ቆይቷል። ይህ ሂደት መጨረሻ ላይ ሁሉንም የአገራችን ህዝቦች እንደማይጠቅም እና ለዘመናት ተከባብሮ እና ተቻችሎ ይኖር የነበረ ህዝባችን በጎ እሴቶቹን የሚንድ ዝንባሌ ነው ብለን እንደ ማሕበር እንምናለን። መንግስት እነዚህን አካሄዶች ለመግታት ጠንክሮ ሊሰራ እንደሚገባ እና በሚያደርገው ህዝብን ያማከለ እንቅስቃሴ ማሕበራችን እንደ ካሁን ቀደሙ ከምን ጊዜውም በላይ አብሮ ለመስራት ዝግጁ ነው። መንግስት እያደረገው ያለው ህዝብን በተለይ ወጣቶችን የሰላምን ጥቅም ለማስተማር የሚደረጉ እና የህዝብ ለህዝብ የሰላም ኮንፈረንሶች በስፋት ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ማሕበራችን ደጋፉን ይገልጻል። የዜጎች ደህንነት በምንም አይነት መልኩ ለድርድር የማይቀርብ መሆኑን ማሕበራችን አበክሮ ያስረዳል። ከዚህ በተጨማሪ የተከሰቱት ችግሮች ምንጭ የሆኑትን ብልሹ አሰራር እና ኪራይ ሰብሳቢነት ላይ መንግስት ትግሉን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪያችንን እናቀርባለን።

በመጨረሻም የህዝቦቻችን አብሮ የመኖር እሴት የሚጻረሩ ቅስቀሳዎች የሚያካሂዱ ተቋማት እና ግለ ሰቦች ማሕበራችን አምርሮ ያወግዛል፤ እንደ ካሁን ቀደሙ አስፈላጊ በኾነ የትግል ስልት እና ሜዳ ሊፋለማቸው ከምን ጊዜውም በላይ ዝግጁ መኾኑን ይገልጻል። መንግስት የህዝብ ሰላም፣ ሕገ መንግስቱን እና የዜጎች ደህንነትን የመጠበቅ ግዴታውን እንዲወጣ ጥሪያችንን እናቀርባለን። በዚህ አጋጣሚ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በተፈጠረ ሁከት ህይወታቸውን ላጡ ዜጎች ማሕበራችን የተሰማውን ሀዘን ይገልጻል።

የትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን ኣሜሪካ
ማእከላዊ ጽህፈት ቤት

ኦክቶበር 26፣ 2017

ዋሽንግተን ዲሲ